HM Government

Grenfell community updates

# Grenfell Tower community update: March 2026 - Amhraic / አማርኛ

**የግሬንፌል ታወር (Grenfell Tower) ማህበረሰብ ወቅታዊ መረጃ፦ ማርች 2026**

ግሬንፌል ታወር በአደጋው ከፍተኛ ጉዳት ለደረሰባቸው ወገኖች ጥልቅ የሆነ የግል ትርጉም እንዳለው እና በታው ለቤተሰቦች የተከበረ መሆኑን እንረዳለን።

ህንጻውን በጥንቃቄ የማፍረስ ሥራችንን በተመለከተ ወቅታዊ መረጃዎችን ልናጋራዎ እንወዳለን። በዚህ ወቅታዊ መረጃ ውስጥ ስለሚከተሉት ጉዳዮች ዝርዝር መረጃ ማግኘት ይችላሉ፦

- **የጣቢያ ደህንነት**
- **የግሬንፌል (Grenfell) የልብ ቅርጽ ባነሮች**
- **የታወሩ መብራቶች**
- **ስለ አቧራ፣ ንዝረት እና ጫጫታ የሚደረግ ክትትል መረጃ**
- **የጤና እና ደህንነት ድጋፍ**
- **እኛን ለማነጋገር ወይም ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት የሚረዱ መንገዶች**

ቀደም ሲል የወጡ መረጃዎችን እዚህ ማግኘት ይችላሉ፦
www.gov.uk/grenfell-community-updates

## የጣቢያ ደህንነት

በዚህ ወር መጀመሪያ ላይ በምዕራብ ለንደን በሌላ የግንባታ ቦታ ላይ ክሬን ከወደቀ በኋላ አንዳንድ ነዋሪዎች በግሬንፌል ታወር ቦታ ላይ የክሬን ደህንነት ጥያቄ እንዳነሱ እናውቃለን። የነዋሪዎች እና በቦታው የሚሰሩ ሰዎች ደህንነት ከፍተኛ ቅድሚያ የምንሰጠው ጉዳይ ሲሆን ይህም በሕግ የተደነገገ ነው። በቦታው ላይ ያሉ ሁሉም መሳሪያዎች በየጊዜው ይመረመራሉ፣ እና የደህንነት ፍተሻዎች በየቀኑ ይከናወናሉ። እባክዎ በዚህ ኢሜይል ያድርጉልን፦ GrenfellTowerSite@communities.gov.uk ማናቸውም ስጋቶች ካሉቡዎት እና ከጣቢያው ቡድን ወይም ከዋናው ስራ ተቋራጭ Deconstruct UK ጋር መነጋገር ከፈለጉ።

## የግሬንፌል የልብ ቅርፅ ያላቸው ባነሮች

የባነር መብራቶች በወሩ መጨረሻ ላይ እንደገና እንዲቀመጡ ይደረጋል፣ በዚህም በባነሮቹ ላይ ወደ ላይ ያበራሉ። ባነሮቹ በጁን ወር ለዘጠነኛው ዓመት በዓል በቦታው ይቆያሉ፣ ከዚያም ይነሳሉ እና ከቀደሙት ስብስቦች ጋር በቦታው ደህንነቱ በተጠበቀ ሁኔታ ይቀመጣሉ።

## የታወሩ መብራቶች

ህንጻው በጥንቃቄ እየፈረሰ ባለበት ወቅት፣ የሚታይ ማስታወሻ መኖሩ አስፈላጊ መሆኑን ሰምተናል። የብርሃን ጨረሮች ፀሐይ ስትጠልቅ ጀምሮ እስከ ምሽቱ 11pm ድረስ በየምሽቱ በታወሩ በእያንዳንዱ ጥግ ላይ ወደ ላይ ማብራት ይቀጥላሉ። በግሬንፌል የልብ ቅርጽ ባነሮች ላይ የሚያበሩት መብራቶች ደግሞ በየቀኑ ጸሐይ ከጠለቀችበት ጊዜ ጀምሮ እስከ 11pm ድረስ ይበራሉ።

## ስለ አቧራ፣ ንዝረት እና የድምጽ ጫጫታ የሚደረግ ክትትል መረጃ

መንግሥት በግሬንፌል ታወር ጣቢያ የሚከናወኑ ማናቸውም ሥራዎች በከፍተኛ ጥራት መከናወናቸውን ለማረጋገጥ ቁርጠኛ ነው።  የማህበረሰቡ እና በጣቢያው ላይ የሚሰሩ ሰዎች ደህንነት እና ጤንነት ሁልጊዜም ቅድሚያ የምንሰጠው ጉዳይ ነው። በጣቢያው ላይ ስለ አቧራ፣ ንዝረት እና የድምጽ ጫጫታ የቀጥታ መረጃዎችን የሚሰበስቡ የክትትል መሣሪያዎች ተተክለዋል። መረጃው በየወሩ ለሕዝብ ይፋ ይደረጋል። የቅርብ ጊዜ ሪፖርቶችን ለማየት፣ እባክዎን ከታች ያሉትን ሊንኮች ይጫኑ፡-

[የአቧራ ክትትል ሪፖርት፡-ከፌብሩዋሪ 2 እስከ ማርች 1፣ 2026]
[የንዝረት ክትትል ሪፖርት፡- ከፌብሩዋሪ 2 እስከ ማርች 1፣ 2026]
[የድምጽ ጫጫታ ክትትል ሪፖርት፡- ከፌብሩዋሪ 2 እስከ ማርች 1፣ 2026]

የእንግሊዝ የጤና ደህንነት ኤጀንሲ (UK Health Security Agency፣ UKHSA) ሥራው በሚካሄድበት ጊዜ በግሬንፌል ታወር (Grenfell Tower) ዙሪያ ያለውን የአየር ጥራት መገምገምና መከታተልን ይቀጥላል። ሪፖርቶቹ በየወሩ ለሕዝብ ይፋ ይደረጋሉ። የቅርብ ጊዜውን ሪፖርት እዚህ ማግኘት ይችላሉ፡- የግሬንፌል ታወር (Grenfell Tower) እሳትን ተከትሎ የሚደረግ የአካባቢ ክትትል - GOV.UK

## የጤና እና ደህንነት ድጋፍ

ህንጻውን በጥንቃቄ የማፍረስ ሥራ በሚከናወንበት ጊዜ ሁሉ፣ ቤተሰባቸውን ላጡ፣ ከአደጋው በሂወት ለተረፉት እና በአቅራቢያው ለሚገኙ ነዋሪዎች የሥነ-ልቦና እና የአካል ደህንነት ድጋፍ መስጠቱ ይቀጥላል። አንድ ሰው ማነጋገር ከፈለጉ፡-

- በ 020 8637 6279 ለግሬንፌል ደህንነት አገልግሎት (Grenfell Wellbeing Service) ይደውሉ (በየቀኑ ከ8am እስከ 8pm)።
- ድንገተኛ ሁኔታ ሲያጋጥም የማዕከላዊ እና የሰሜን ምዕራብ ለንደን የኤን ኤች ኤስ ፋውንዴሽን ትረስት (Central and North West London NHS Foundation Trust's, CNWL) የአንድ ጊዜ የምክር አገልግሎት መስመርን በሚከተለው አድራሻ ይደውሉ፡-
  0800 0234 650 (በቀን ለ24 ሰዓታት፣ በሳምንት ለሰባት ቀናት ክፍት ነው)።
- ኢሜል: grenfell.wellbeingservice@nhs.net
- ተጨማሪ ለማወቅ እዚህ ይጎብኙ፡- www.grenfellwellbeing.cnwl.nhs.uk

ስለሚገኙ አገልግሎቶች የቅርብ ጊዜ መረጃ ለማግኘት የሚከተለውን ይጎብኙ፡- www.grenfell.nhs.uk

## እንዴት ማነጋገር ወይም ተጨማሪ መረጃ ማግኘት እንደሚቻል

መረጃውን ለእርስዎ ጠቃሚ በሆነ መንገድ ማጋራት እንፈልጋለን። በሚከተሉት አድራሻዎች ላይ በየጊዜው የሚወጡ ዝማኔዎችን እና መረጃዎችን ማጋራታችንን እንቀጥላለን፡-
www.gov.uk/grenfell-community-updates

እባክዎ በዚህ ኢሜይል ያድርጉልን፦ GrenfellTowerSite@communities.gov.uk ወደ:

- እኛን ወይም የግሬንፌል ታወር ጣቢያ፣ ዋና ስራ ተቋራጬን DCUK ለእርስዎ ምቹ እና ተመራጬ ሰዓት፣ ቀን እና በታ ለማነጋገር ቀጠሮ ይያዙ።
- ህንጻውን በጥንቃቄ የማፍረስ ሥራን በተመለከተ ያሉዎትን ማናቸውንም ጥያቄዎች ይጠይቁን ወይም ስጋቶችዎን ያጋሩን።
- የምናወጣቸው ወቅታዊ መረጃዎች በቀጥታ በኢሜይል እንዲላኩልዎ ይጠይቁን።
- ከእርስዎ ጋር በምናደርገው የግንኙነት እና የተሳትፎ ሂደት ላይ ያለዎትን አስተያየት፣ ፍላጎትዎ ከሆነ፣ ያጋሩን። የእርስዎን ሃሳቦች በደስታ እንቀበላለን።

ስለ ግሬንፌል ታወር (Grenfell Tower) የቅርብ ጊዜ መረጃዎችን ለማግኘት እና የኢሜይል ማሳወቂያዎች እንዲደርስዎ ለመመዝገብ፣ እባክዎን ወደ www.gov.uk/grenfell-community-updates ይሂዱ ወይም የQR ኮዱን ይቃኙ።